# የአመለካከቱን “እምቦጭ”ስ እንዴት እናጥፋው?

**አሸናፊ መለሰ 10-10-17**

የአንድ ሀገር ህልውና በዋናነት በህዝቦቿ የእርስ በርስ መተማመን፣ የእርስ በርስ መከባበርና ፍቅር እንዲሁም በታሪክ አጋጣሚዎች ለሚከሠቱ ውጣ ውረዶች እንደአንድ ሆኖ በሚሠጥ ምላሽ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያም እንደሃገር የዛሬዋ ቀን ላይ ለመድረስ የቻለችው የተባበረ ህዝብ ባለቤት፣ የተከባበሩ የህዝቦች ምድርና ጠንካራ ሀገራዊ ስሜትን መፍጠር የሚያችሉ ልዩ ልዩ ባህሎች መገኛ ከመሆኗ ላይ ነው፡፡ በዚህ የሀገር ፍቅር የተሟሸ ማህፀኗም ዘወትር ጀግኖችን ማፍራት የማይሳነው በመሆኑ ለጠላቶቿ መቃብር፣ ለወዳጆቿ የመንፈሳዊ ገነት ለመሆን ችላለች፡፡

ሀገራችን የግሪክ አማልክት ውብ መዳረሻ ከመሆንም አልፋ አማልክቱ በውብ ልጆቿ ፍቅር ከንፈውና ተዋልደው እስከመኖር መብቃታቸውን ከጥንታዊ የግሪክ አፈ-ታሪኮች ለማንበብ ይቻላል፡፡ ለአብነትም የግሪኩ ጣኦት ቲዎነስ ከኢትዮጵያዊቷ ኢዎስ ሜምኖን የተባለ ንጉስ ስለመውለዱ ተተርኳል፡፡ ሜምኖን በዘመኑ ከታላቁ ጦረኛ ጣኦት አኪለስ ያልተናነሠ የውጊያ ብቃት ያለው ከመሆኑም ሌላ በትሮይ ጦርነት ጦሩን ይዞ ተሳትፎ ታላቅ ጀግንነትን እንደፈፀመ በበርካታ የአፈ-ታሪክ ድርሳኖች ተወስቷል፡፡

እንኳን የአፍሪካን የህንድን ስልጣኔና ሀይማኖት የፈጠሩ፣ በስነፈለክ፣ በሂሳባዊ ቀመር፣ በስነፅሁፍና ኪነህንፃ በስልጣኔ ጫፍ ላይ የደረሱ ህዝቦችን የፈጠረች ናት ሀገራችን፡፡ በዘመናችን የስልጣኔ ሚዛን ሊሠፈሩ የማይቻላቸው፣ በዛሬው የባህልና ፍልስፍና ቅንብብ ውስጥ ለመቀመጥ አጥሩ የማይመጥናቸው የሠብዓዊ ስልጣኔና የዳበረ ባህል ባለቤትም ናት እናታችን፡፡ ተመርምረው የማያልቁ የስነፅሁፍ ሃብቶች፣ ታይተው የማይጠገቡ ባህላዊ ሁነቶች፣ ተቆጥረው የማያልቁ የተፈጥሮ ሃብቶች፣ ተዳስሠው የማያበቁ ጥበባዊ ሃብቶች፣ ታስበው የማያልቁ “ኢትዮጵያዊ” ፍልስፍናዎች ባለቤት ናት መገኛችን፡፡

እነዚህ ሁሉ የታሪክ ሂደቶችና ሀብቶች ያለእንቅፋት የተገኙ፣ ያለኮሽታ እውን የሆኑ አልነበሩም፡፡ በየዘመኑ ዘመን ያሳበጣቸው በርካታ ተስፋፊዎችና ወራሪዎች በመልከዓምድሯ ማማር፣ በመልከዓምድራዊ አቀማመጧ ስትራቴጂያዊነትና ባላት የተፈጥሮ ሃብት ጉምዥት ውስጥ ገብተው ምድሯን የራሳቸው ለማድረግ ለበርካታ አመታት ዘመናቸው የሠጣቸውን ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረጉ የሃይል የወረራ ሙከራዎችን አድርገዋል፡፡ የእነዚህ ሙከራዎች ውጤት በሠው ህይወትና በኢኮኖሚያችን ላይ

መንሸራተትን ቢያስከትልም የወራሪዎቹ ሙከራ ሁሉ በሽንፈት የተጠናቀቀ በመሆኑ በአንድ በኩል ሀገራችንን በታሪክ ማህደር የጀግኖች ሃገር ሲያስብላት፣ በሌላ በኩል የተገኙ ድሎች በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ ያለንን መተማመን እንድናሳድግና እንደአንድ ታላቅ ህዝብ የራሳችን የሆነ ምንትነት (Identity) እንዲኖረን አስችሏል፡፡

እነዚህ አደጋዎች ከውጪ ይምጡ እንጂ ኢትዮጵያውያን በገዛ ገዢዎቻቸው ከባርነት ባልተናነሠ ጭቆና ውስጥ ያለፉባቸው አጋጣሚዎችም ነበሩ፡፡ እነዚህ ጭቆናዎችን ተከትሎም ህዝቦችን የስልጣን ባለቤት ለማድረግ፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እንዲሠፍንና ድህነትን ማጥፋት እንዲቻል፣ እንዲሁም በመከባበርና በፍቅር ላይ የተመሠረተውን አንድነት ለማፅናት በርካታ ዘመናትንና በርካታ መስዋዕትነትን የጠየቁ መራር ትግሎች ተካሂደዋል፡፡

ይህ ትግል ፍሬ አፍርቶም የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ለመፍጠር ተችሏል፡፡ ይህ ስርዓት ፌዴራሊዝምን እንደዋነኛ የስርዓት መመስረቻ ርዓዮተ ዓለሙ አድርጎ እንደመዋቀሩ፣ ፌዴራሊዝም በተለይም የተለያየ ቋንቋን፣ የተለያየ ባህልንና ማንነትን ለሚያንፀባርቁ የአንድ ሀገር ህዝቦች መፈቃቀድን መሠረት ያደረገ፣ ልዩነትን የውበትና የመቻቻል መከሠቻው ያደረገ፣ የራስን እድል በራስ የመወሠንን መብት የሠጠ መንግስታዊ አደረጃጀትን ለመፍጠር ወሳኝ በመሆኑ አዋጪነቱ ላይ አውቆ ለተኛው ካልሆነ በስተቀር ጥያቄ የሚያስነሳ አይመስለኝም፡፡ በመሆኑም በዚህ የአስተዳደር ርዕዮት ጥላ ስር ሆነን በአንድ በኩል የጀመርነውን የልማት ተጋድልኦ በስፋት ማስኬድ፣ በሌላ በኩል ስርዓቱ በሠጠን መልካም አጋጣሚ መነሻነት በስርዓቱ ውስጥና ከስርዓቱ በተፃራሪ በቆሙ ሃይሎች የሚታዩ የፀረ ዴሞክራሲ አመለካከትና ተግባራት ላይ፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ላይ የጋራ ክንዳችንን ማንሳት ይገባናል፡፡

ከሠሞኑ፣ በተለይም በኦሮሚያና ሶማሌ ክልሎች ድንበር አካባቢ የተነሱ የይገባኛል ግጭቶችን መሠረት አድርገው እየታዩ ያሉ ፀረህዝብ እንቅስቃሴዎች የህዝቦችን አብሮ የመኖር ታሪክ በማጠልሸት፣ በህዝቦች መተላለቅና ትርምስ መሃል ትርፋማ ለመሆን የሚውተረተሩ ሃይሎች ተጋድልኦ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ እነዚህ እኩይ ወገኖች በአካባቢው የተከሠተውን ግጭት የብሄሮች ጦርነት ለማስመሠል ከሚያደርጉት ጥረት ጎን ለጎን ራሳቸውን የሠብዓዊ መብት ተሟጋች ለማድረግ እያደረጉት ያለው ሙከራ በጣም አስገራሚ ነው፡፡

ለመሆኑ እነዚህ ወገኖች ያሠቡት ቢሳካላቸውና የብሄሮች የርስ በርስ ግጭት ቢከሠት የሚያተርፉት ምንድን ነው? በሠዎች ሞት የሚገኝ የፖለቲካ ትርፍስ እስከምን ያደርሳቸዋል? ሰው ተላልቆ ሲያበቃ በየትኛው ሜዳ ላይ ለመንገስ ነበር እንዲህ ነጋሪት ለመጎሠም ሲቋምጡ የታዩት?

እንደእውነቱ ከሆነ ይህን መሠል እኩይ አመለካከት ሊመጣ የሚችለው በአስተሳሰብ ላይ ከሚከሠት "እንቦጭ" የመሰለኛል፡፡ ይህ እንቦጭ በአንድ በኩል የኔ ብቻ ታላቅ፣ የኔ ብቻ ሁል ጊዜ ትክክል እና እኔ አልጎዳ እንጂን ከመሠሉ የአመለካከት መመረዞች የሚመነጭ ይመስለኛል፡፡ ራሱን ፍፁም ትክክል አድርጎ የሚያስብ ለለውጥ የተዘጋጀ አይደለም፡፡ እኔ ብቻ ልክ የሚል ውስጡ በአጓጉል የትዕቢትና የአላዋቂነት ጭቃ የተሞላ ነው፡፡ እኔ ብቻ ታላቅ ነኝ የሚል የራሱን የታላቅነት ካባ ያበጀው ሌሎችን በንቀት ከመፍተል ባገኘው እኩይ ድርና ማግ ነው፡፡ እኔ አልጎዳ እንጂ ባይ የእሳትን መፋጀት በተረት እንጂ በተግባር ያልተመለከተ ነው፡፡ እኔን ካልነካ ምን አገባኝ የሚል እውነተኛ አድራሻው የፌስቡክ መንደር ነው፡፡

በአንድነት በሚኖሩ ህዝቦች መካከል ፍቅር እንዳለ ሁሉ ጠብም ይኖራል፡፡ ይህ የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ በዘመናት የህዝቦች የኑሮ እንቅስቃሴ ውስጥ ጠብ የፍቅርን ያክል ባይሆንም መከሠቱ ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ዋናው ነገር የተፈጠረውን ጠብ እንዴት መፍታት ይችላሉ ነው፡፡ እንደእድል ሆኖ ሀገራችን ይህን መሠል የድንበር ግጭት ሲነሳ ግጭቱን ለማከሠም የሚያስችሉ አያሌ ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ ይትባህሎች ባለቤት መሆኗ ነው፡፡ እነዚህ የግጭት መፍቻ ባህሎች እንደዘመናዊ ፍርድ ቤት "እግድ" "አፈፃጸም"ና "ይግባኝ" ሳያስፈልጋቸው በውይይት ተጀምረው በጭፈራ የሚጠናቀቁ ስለመሆናቸው ድርሳን መግለጥ አያስፈልገንም፡፡

በመሆኑም መንግስት እነዚህ የተነሱ ግጭቶችን ለማብረድ እያደረገ ካለው ጥረት ጎን ለጎን እነዚህን የፀረሠላም ሃይሎች መታገልና ለፍርድ ማቅረብ ይገባዋል፡፡ በተለይም ከሰሞኑ መንግስት ራእዩን ያስፈፅሙልኛል ብሎ በሾማቸው ሹማምንት ጭምር እየተሠማ ያለው ፀረ ሠላም መግለጫ የተፈጠረውን ግጭት ከማባባስና በህዝቦች መካከል የተፈጠረውን መተማመን ከመሸርሸር አንፃር ጉዳቱ የከፋ በመሆኑ አፋጣኝ እርምጃ መውሠድ ለነገ የሚተው የቤት ስራ መሆን የለበትም፡፡  በሌላ በኩል ህዝቡ እነዚህን እኩይ ስብከቶች በጥንቃቄ በማጤን የአፍራሽነታቸውን ልክ በሚገባ መረዳትና ማውገዝ ይገባዋል፡፡

ከሠሞኑ በጣና ሃይቅ ላይ የተከሠተውን እንቦጭ ለማጥፋት መላው የክልሉ ህዝብም ሆነ የመሃል ሀገር ወጣቶች ጭምር ሰፋፊ ዘመቻዎችን ማዘጋጀታቸውን እያየንና እየሠማን ነው፡፡ እነዚህ ወጣቶች ያንን ፀረ

ሃይቅ አረም ለማጥፋት በድፍረት እንቦጩ ወደሚገኝበት ሃይቅ ገብተው አረሙን ከስሩ ሲመነግሉት፣ ቀስ በቀስ ከተቆጣጠረው ግዛቱ ሲያስወግዱት ተመልክተናል፡፡

ይህ የፀረ እንቦጭ እንቅስቃሴ ለዚህ የድንበር ግጭትም ሆነ የፀረ ህዝብ እንቅስቃሴዎች የሚያስተምረው ነገር አይጠፋም፡፡ ይህን ፀረህዝባዊ አስተሳሰብ ከስሩ ለመመንገል ምን ማድረግ አለብን? የህዝቦችን አብሮ የመኖር ባህል ለማጥፋት፣ በህዝቦች ትርምስ ለማትረፍ የቋመጡ የማህበራዊ ሚዲያ ጀብደኞችን እንዴት እንዋጋቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች የፀረ እንቦጭ ዘመቻው መልስ ያለው ይመስላል፡፡

ወደድንም ጠላንም ሌላ ሀገር የለንም፡፡ በመሆኑም ያለን ብቸኛ አማራጭ ይህችኑ ሀገራችንን መጠበቅ ነው፡፡ ሃገር የምትጠበቀው ከውጪ ጠላት ብቻ ሳይሆን በተለያየ ምክንያት ወደጥፋቷ ከሚመሯት የገዛ ልጆቿም ጭምር መሆኑን ማስተዋል ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ይህችኑ ሀገራችንን በቻልነው ልክ ማሳደግ ያስፈልገናል፡፡ ድህነታችን ከሀገራት ጭራ አስቀርቶ የጠለሸ ስም ያሠጠን ጠላታችን ነውና ልንፋለመው ግድ ይለናል፡፡ ይህ የፀረ ድህነት ትግል በመንፈሳዊ ልማት፣ በማህበረሠብ ልዕልና፣ በቁሳዊ እድገትና በአስተሳሰብ ተራማጅነት ሁሉ አቀፍ ሆኖ መቀጠል ይገባዋል፡፡ እነዚህ ህዝባዊ ትግሎች የሠሞነኛውን የፀረ ህዝብ አመለካከት አራማጆች አመለካከት በማቅለልና የህዝቦችን የግንዛቤ አቅም በማስፋት እነዚህን ለመሠሉ አስተሳሰቦች ቦታ የማይሠጥ ትውልድ ለመፍጠር ወሳኝ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በአንፃሩ የእነዚህን እኩይ “ነብያት” ሴራ ለማክሸፍ በተገኘው መድረክ ሁሉ መታገል ተገቢ ነው፡፡ የጦርነት አታሚቻውን በሚነስሙበት የማህበራዊ ድረገፆች ላይም እውነተኛውን መረጃ በማሠራጨትና ሃሣብና ሀሳብን ብቻ የያዙ ውይይቶችን በማድረግ የሃሳብ የበላይነትን መያዝ ያስፈልጋል፡፡

ጣና በእንቦጭ እንደማይዋጥ ሁሉ ሀገርም በእኩይ አስተሳሰብ አትፈርስም፡፡ ለዘመናት በፍቅር የኖረን ህዝብ ለማፋጀት በፌስቡክ የሚነሠም ነጋሪት ከፌስቡክ ሜዳ ርቆ አይሠማም፡፡ ህዝቦቻችን ውበታችንና መከታችን ሆነው ዝንታለም አብረው ይኖራሉ፡፡